# ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ

ሕዳር 11 ቀን 2014

<u>አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ</u>

# የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ

## የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ

### መግቢያ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የሚካሄደው በባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን የኩባንያው መልካም አስተዳደር ከሚገለፅባቸው መንገድ አንዱ የዳይሬክተሮች ምርጫ ሂደት ግልጽነት የተላበሰ እንዲሆን ማስቻል ነው። የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫን ለማከናወን የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ በኩባንያው መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የማይተካ ሚና አለው። የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴውም የተሻለ የአመራር ብቃት እና ሀቀኝነትን የተላበሱ እጩ ዳይሬክተሮች እንዲመረጡ በማድረግ ተመራጮችም የኩባንያውን አስተዳደር በመምራት የኩባንያውን ጥቅም እንዲያስጠብቁ ያስችላል።

በዚህም መሠረት የባለአክስዮኖችን ጠቅላላ ጉባዔ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ የሚመርጥበትን አካሄድ፣ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴውን የሥራ ሂደት ደንብ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ ቀጥሎ እንደተመለከተው ፀድቋል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ **"የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1.1 **ትርጉም**

- **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።
- **"ዋና ሥራ አስፈፃሚ ማለት"** የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ. ዋና ሥራ አስፈፃሚ ማለት ነው።
- **"ዳይሬክተር"** ማለት ማናቸውም የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ የቦርድ አባል ማለት ነው።
- **"ሠራተኛ"** ማለት በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ በኩባንያ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው።
- **"ጠቅላላ ጉባዔ"** ማለት የኩባንያው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው።
- **"ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክስዮን"** ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኩባንያው የተፈረመ ካፒታል 2% (ሁለት በመቶ) እና ከእዛ በላይ የሆነ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ነው።

- **"ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን"** ማለት "ከኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ ከ2% በታች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው።
- **"አስመራጭ ኮሚቴ" ወይም "ኮሚቴ:"** ማለት "የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ" ነው።
- **"ኩባንያ"** ማለት የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ ማለት ነው።

## 2. <u>የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

2.1 በሥራ ላይ ያለው ቦርድ የሥራ ጊዜ ከማለቁ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ የኩባንያው ባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ መምረጥ አለበት።

2.2 አስመራጭ ኮሚቴውን የመምረጥና ኮሚቴው የሚመራብትን የአሰራር ስርዓት (ደንብ) የማፅደቅ ኃላፊነት የጠቅላላ ጉባዔው ነው።

2.3 ጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡትን የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ሚስጥራዊ በሆነ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ይመረጣል።

2.4 በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡት የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው አባላት ብዛት 5 (አምስት) ናቸው።

2.5 ጠቅላላ ጉባኤው በቅድሚያ 10 (አሥር) ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በመጠቆም ከዚህ ውስጥ በሚያገኙት ድምፅ ብዛት መሠረት 5 (አምስቱ) የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ሆነው እንዲሰሩ ይመርጣል።

2.6 ለአስመራጭ ኮሚቴ አባልነት ከተመረጡት በተጨማሪ 2 (ሁለት) ተጠቋሚዎች ባገኙት ድምፅ መሠረት በተጠባባቂነት ይያዛሉ።

2.7 የምርጫው ውጤት ምርጫው በተካሄደበት ቀን ለጉባኤው ይገለፃል።

2.8 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የሥራ ዘመን ከተመረጡበት ቀን ጀምሮ የተመራጮቹ የቦርድ አባላት ምርጫ ውጤት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እስኪፀድቅና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እስኪመዘገብ ድረስ ብቻ ይሆናል።

2.9 ይሁንና የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ሥራውን የሚጀመረው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ከመካሄዱ ስድስት ወራት በፊት ነው።

## 3. <u>የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት</u>

3.1 ለምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት የሚመረጡ የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

- የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ተብሎ በወጡ የወንጀለኛ መቅጫ ህጎች ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር በማታለል ወይም እምነት በማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ያልሆኑ።

- ሁሉም የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት የኩባንያው ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸው።
- የልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በፍላጐታቸው የተመረጡ መሆን አለባቸው።
- የኩባንያው ሠራተኛ የሆነ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባል ሆኖ መመረጥ አይችልም።
- ቢያንስ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ወይም ከዚህ ጋር አቻ የሆነ የትምህርት ደረጃ ያጠናቀቁ መሆን ይኖርባቸዋል።

3.2 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ሆነው ከሚመረጡ አባላት መካከል ቢያንስ ሁለቱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸው።

3.3 በሥራ ላይ ያሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም።

3.4 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ከአባላቱ መካከል ሊቀመንበር እና ፀሐፊ ይመርጣል።

3.5 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ስለዚህ የአሠራር መመሪያ በኢንሹራንስ ኩባንያው በሚዘጋጅ መርሐ ግብር ሥልጠና መውሰድ ይገባቸዋል።

## 4. <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት</u>

በሥራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

- የምልመላና የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ እንዲመረጡ የማስደረግ፣
- የጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ ሲያዝ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ ስለመኖሩ በአጀንዳ መያዝ፣
- የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ከተመረጠ በኋላ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ አስፈላጊውን አጋዥ ሠራተኛ፣ የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ።

## 5. <u>የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ኃላፊነት</u>

የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- በመጀመሪያው የስብሰባው ዕለት የኮሚቴውን ሊቀ-መንበር እና ፀሐፊ ይመርጣል።
- የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና ምርጫ ሂደትን በአግባቡ የማካሄድ እና በጸደቀው የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና የምርጫ አፈፃፀም (መመሪያ ማሻሻያ 1) ላይ በሚዘጋጀው ስልጠና ላይ መገኘት።
- የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን የመመልመልና እና የማስመረጥ ሂደት ኃላፊነት አለበት።
- የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ምርጫም ሆነ የዳይሬክተሮች ሹመት ግልፅነትና ተአማኒነት ባለው አኳኋን መካሄዱን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች፣ በሀገሪቱ ህግና በዚህ ደንብ መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት።

## 6. የምልመላና የአስመራጭ ኮሚቴ የአሠራር ደንብ

6.1 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የሚሰበሰብበትን ቀን፣ ጊዜ እና ቦታ በራሱ ይወሰናል እንዲሁም መደበኛ ስብሰባዎች ይኖሩታል፡፡

6.2 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኮሚቴውን ድንገተኛ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

6.3 ከግማሽ በላይ የሆኑ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሟላል፡፡

6.4 የኮሚቴው ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው በአባላቱ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል፡፡ ሆኖም እኩል ድምፅ ሲኖር ሰብሳቢው የመጨረሻ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

6.5 የኮሚቴው ሰብሳቢ ስብሰባ የመጥራት፣ ስብሰባውን የመምራት ፣ አጀንዳ የመቅረፅ እንዲሁም ኮሚቴውን በመወከል ግንኙነቶች የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፤ ፀሀፊው የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

6.6 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የሚያሳልፉቸውን ውሳኔዎች በቃለ-ጉባኤ መያዝ ያለበት ሲሆን፣ ቃለጉባኤውም በስብሰባ በተገኙ አባላት መፈረም አለበት፡፡

6.7 ከምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው አባላት መካከል ቁጥራቸው ከግማሽ (50%) በታች የሆኑት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በዚህ ህግ መሠረት ሳይወጡ ሥራውን ቢለቁ የተቀሩት አባላት በምትካቸው በተጠባባቂነት ከተያዙት መካከል በኮሚቴው ምሥረታ ወቅት ባገኙት የድምፅ ቅደም ተከተል መሠረት ይተካሉ፡፡

6.8 በሥራ ላይ ያለው የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከግማሽ (50%) በታች በሆነ ጊዜ ከተጠባባቂዎቹ ውስጥ የሚተኩበት አግባብ አይኖርም፡፡ ሆኖም ግን ቀሪዎቹ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ጉዳዩን በሥራ ላይ ላለው የዳይሬክተሮች ቦርድ በማሳወቅ ሥራውን መተው አለባቸው፡፡

6.9 በተራ ቁጥር 6.8 መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ስራውን ከተወ በስራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ይህንኑ ሁኔታ ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ማድረግና ጉዳዩን አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች በተደነገገው መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ በተደነገገው መሰረት ጠቅላላ ጉባኤው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲመረጡ ያደርጋል፡፡

6.10 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ሃላፊነቱን ግልፅነት በተሞላበት፣ በአግባቡና እምነት በሚጣልበት መልኩ ሳያከናውን ከቀረ እና በብሔራዊ ባንክ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች እና በኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ የተመለከቱትን ሳይከተል ቀርቶ የምርጫው ውጤት ከተሰረዘ ለኮሚቴው ከሚከፈል ክፍያ በማይበልጥ መቀጮ የሚቀጣ ይሆናል፡፡

## 7. የዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ አቀባበል ሂደት

7.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ባለአክስዮኖች ለዳይሬክተሮች ቦርድ የእጩዎች ጥቆማ መጀመሩን ስፊ ስርጭት ባለው የህትመትና ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ብዙሃን ጥሪ ማስተላለፍ አለበት፤ ባለአክስዮኖች የእጩዎች ጥቆማ እንዲያደርጉ መጋበዝ አለበት፡፡

7.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ጥሪውን ሲያስተላልፍ እጩ ተጠቋሚዎች ማሟላት የሚገባቸውን ዝቅተኛ መመዘኛዎች እና ጥቆማው የሚቀርብበትን ፎርም ማሳወቅ አለበት፡፡

7.3 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የጥቆማ መቀበያ ጊዜ የሚያበቃበትን ቀን መወሰን አለበት፤ ሆኖም ለጥቆማ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ ከሦስት ወር ያነስ መሆን የለበትም፡፡

7.4 የምልመላና የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ለዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠቋሚ እጩ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

7.5 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ጊዜያዊ ቢሮ እና ጊዜያዊ ሠራተኞችን በመያዝ ሥራውን ሊያከናውን ይችላል፡፡ ኮሚቴው መዝገብ በማዘጋጀት የተጠቋሚ ዕጩዎችን ስምና አስፈላጊ መረጃዎችን በመዝገቡ ያሰፍራል፡፡

7.6 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የተሻለና አመቺ መስሎ በታየው የግንኙነት አግባብ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከሚካሄድበት ዕለት አስቀድሞ ባሉት ጊዜያት ሁሉም ባለአክስዮኖች ብቃት ያላቸው እጩዎች እንዲጠቁሙ የሚያስችል መንገድ በማመቻቸት ባለአክሲዮኖች ዕጩዎችን እንዲጠቁሙ እድል መስጠት አለበት፡፡

7.7 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ለምርጫ ከሚያቀርባቸው ተጠቋሚ እጩዎች መካከል የሚከተሉት መስፈርት መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. ከተጠቋሚ እጩዎች መካከል 1/3ኛው ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ የተጠቆሙ እና የሚመረጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ተብለው የሚወሰዱት ባለአክስዮኖች ከኩባንያው የተፈረመ ካፒታል ቢያንስ 30 በመቶ ድርሻ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ከእጩ ተጠቋሚዎች መካከል 1/4ኛው እጩ ተጠቋሚዎች ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ የተጠቆሙ እና የተመረጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች ተብለው የሚወሰዱት ባለአክስዮኖች ከኩባንያው የተፈረመ ካፒታል 30 በመቶ በታች ድርሻ መያዝ ይኖረባቸዋል፡፡

ሐ. የተቀሩት 2/3ኛው ወይም 3/4ኛው ተጠቋሚ እጩዎች ደግሞ መጠቆምና መመረጥ ያለባቸው በሁሉም ባለአክሲዮኖች ነው፡፡

7.8 ከላይ በተራ ቁጥር 7.7 ላይ የተጠቀሰውን ስብጥር ለመጠበቅ 2/3ኛ (ወይም 3/4ኛ) እጩ ተጠቋሚዎች በሁሉም ባለአክስዮኖች ከተጠቆሙት እጩዎች የሚወሰዱ ሲሆን ቀሪዎቹ 1/3ኛ (ወይም 1/4ኛ) ደግሞ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ብቻ ይወሰዳሉ፡፡

7.9 በተራ ቁጥር 7.8 የተጠቀሰውን ስብጥር በባለአክስዮኖች የእጩዎች ጥቆማ ወቅት ካልተጠበቀ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ይህ ስብጥር እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ተገቢውን ስብጥር ለመጠበቅ ኮሚቴው በቅድሚያ 1/3ኛውን (ወይም 1/4ኛውን) ተጠቋሚዎችን ከለየ በኃላ 2/3ኛውን (ወይም 3/4ኛውን) ደግሞ በሁሉም ባለአክሰዮኖች ከተጠቆሙት ይወስዳል፡፡ ይህንኑ ስብጥር ለማረጋገጥ ኮሚቴው በመጀመሪያ 1/3ኛውን (ወይም 1/4ኛውን) እጩ ተጠቋሚዎችን ከለየ በኂላ ወደ 2/3ኛው (ወይም 3/4ኛው) እጩ ተጠቋሚዎች ያመራል፡፡

7.10 የእጩ ቦርድ ተጠቋሚዎች ብዛት 18 (አሥራ ስምንት) ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ ኮሚቴው 4(አራት) ተጠቋሚዎችን ለመምረጥ ፈቃደኛ ባልሆኑ እጩዎች ቦታ ለመተካት በተጠባባቂነት ይይዛል፡፡

7.11 ኮሚቴው የተጠቋሚዎችን ምርጫ የሚያካሄደው ተጠቋሚዎቹ ባገኙት የድምፅ መጠን ሲሆን፣ ድምጹም የተፈረመ የአክሲዮን መጠን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡ በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ከአንድ በላይ ዕጩዎች እኩል ድምፅ ያገኙ እንደሆነ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የተሻለ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና ሌሎች ለውድድሩ ጠቃሚ ተብለው በሚታሰቡ መስፈርቶች አብላጫ ያለውን እጩ ይወስዳል፡፡

7.12 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የመረጣቸውን የቦርድ ዕጩዎች ዝርዝር በሚከተሉት ሁኔታዎች መግለፅ አለበት፡፡

- በኩባንያው ዋና መ/ቤትና በሁሉም ቅርንጫፎች ሁሉም ሰው በሚያየው ቦታ እንዲለጠፍ ያደርጋል፡፡
- ሰፊ የስርጭት ሽፋን ባላቸው ጋዜጦች እንዲወጣ ያደርጋል፡፡
- በኩባንያው ድረ-ገፅ ላይ ያወጣል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤው ከመካሄዱ ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት ተፈፃሚ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

7.13 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የዕጩ ተጠቋሚዎችን ዝርዝር ከታች ከተዘረዘሩት የእያንዳንዱ እጩ ዝርዝር መረጃ ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡-

- የእጩውን ስም እና ዕድሜ፣
- የትምህርት ደረጃ፣
- የሥራ ልምድ፣
- ያገኘው የጥቆማ ድምፅ ብዛት፣
- በጊዜው ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት

7.14 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩ ተጠቋሚዎችን አስመልክቶ የሚሰጣቸው የድጋፍ ሃሳቦች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች ከተቀመጡ መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

7.15 የቀረቡ ተጠቋሚ እጩዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሳያሟሉ ሲቀሩ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የተሻለ አማራጭ ሆኖ በሚያገኘው መንገድ መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ተጠቋሚ ዕጩዎች ቁጥር የሚያሟላበት ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ማድረግ አለበት። ይህን ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ግን ኮሚቴው ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባኤው አሳውቆ በጠቅላላ ጉባኤው ማስመረጥ አለበት።

## 8. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደት

8.1 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ከጉባኤው ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደትን የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።

8.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ እጩ ተጠቋሚዎችን ከተገቢ መግለጫ ጋር ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል።

8.3 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ተጠቋሚ እጩዎች ራሳቸውን ለጠቅላላ ጉባኤው እንዲያስተዋውቁ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት እንዲገልፁ እድል መስጠት አለበት።

8.4 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው የኩባንያው አካላት ጋር በመተባበር የድምጽ መስጫ ካርድ እና የድምፅ መቀበያ ሳጥኖችን ያዘጋጃል።

8.5 የድምፅ መስጫ ካርዱ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት።

- የባለአክሲዮኑ ስም፣
- የባለአክሲዮኑ የተፈረመ የአክሲዮን ድርሻ፣
- የባለአክሲየኑ መለያ ቁጥር (የመዝገብ ቁጥር)፣
- የኩባንያው ስም እና አርማ፣
- የኩባንያው ማህተም፣ እና
- ባለአክስዮኑ ሊመርጠው የሚፈልገው የእጩ ተጠቋሚ ስም የሚፃፍበት ቦታ።

8.6 ባለአክስዮኖች በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የመገኘት ፊርማ በሚፈርሙበት ጊዜ የድምፅ መስጫ ካርዶች ለባለአክስዮኖች ይሰጣል። በተጨማሪም የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የምርጫ ሂደቱን በቅርበት መከታተል ይኖርበታል።

8.7 ከእጩ ተጠቋሚዎች መካከል የቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ ፈቃደኛ የማይሆን ቢኖር ወይም በሌላ ምክንያት ጥቆማው ተቀባይነት ካላገኘ በተጠባባቂነት ከተያዙት እጩ ተጠቋሚዎች በቅደም ተከተል በመተካትና ተመሳሳይ ስነ-ስርዓትን በመከተል ምርጫው እንዲካሄድ ይደረጋል።

## 9. የድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

9.1 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ለምርጫው የሚያስፈልጉ የድምፅ መስጫ ሳጥኖችን ያዘጋጃል።

9.2 ባለአክሲዮኖች በድምፅ መስጫ ካርዱ ላይ የሚመርጡትን እጩ ስም በመፃፍ ድምፃቸውን ከሰጡ በኋላ ካርዱን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው የድምጽ መስጫ ሣጥን ውስጥ ያስገባሉ፡፡

9.3 ባለአክሲዮኖች በአካል በመገኘትም ሆነ በውክልና የሚያከናውኑት የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በኩባንያው መመሥረቻና መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መከናወን አለበት፡፡ ሆኖም ባለአክሲዮኖች የራሳቸውን ጨምሮ በውክልና የሚይዙት ድምፅ ከኩባንያው የተፈረመ ካፒታል ከ10 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

9.4 የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ አስመራጭ ኮሚቴው ከጉባኤው ፅ/ቤት እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር በመሆን የድምፅ ቆጠራ ያካሂዳል፡፡

9.5 የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ እጩ ተመራጭ የተሰጠውን ድምፅ እና ውድቅ የተደረጉ የድምፅ መስጫ ካርዶችን መመዝገብ አለበት፡፡ በተጨማሪም ውድቅ የተደረጉ የድምፅ መስጫ ካርዶች ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በካርዱ ላይ ተፅፎ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው ሊፈርምበት ይገባል፡፡

9.6 የድምፅ መስጫ ካርዱን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውድቅ ያደርጋል፡፡

- የባለአክሲዮን ስም ያልተፃፈበት ከሆነ፣
- የባለአክሲዮኑ የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት ያልተፃፈበት ከሆነ፣
- የኩባንያው ስም እና አርማ ያልታተመበት ከሆነ፣
- የዕጩ ተመራጭ ስም ያልተፃፈበት ከሆነ፣
- የድምፅ መስጫ ካርዱ ፊርማ የሌለበት ከሆነ፣
- የድምፅ መስጫ ካርዱ ስርዝ ድልዝ ያለበት ከሆነ፣ እንዲሁም
- የባለአክስዮኑን የመለያ ቁጥር ወይም የምርጫ ቁጥር የማያመላክት ከሆነ፡፡

9.7 የድምፅ ቆጠራው ሲጠናቀቅ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቱ እንዲሁም የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ስለመሆኑ በቃለጉባዔ ተይዞ ለዚሁ በተዘጋጀ ፎርም ላይ በመፈረም ማረጋገጥ አለበት፡፡

9.8 ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጠውና የተቆጠረው ድምፅ ታሽጎ ለብቻ መቀመጥ አለበት፡፡

9.9 የድምፅ ቆጠራው ውጤት ድምፅ በተሰጠበት ቀን ለጠቅላላ ጉባኤው ይገለፃል፡፡ ይህን ማድረግ የማይቻል ከሆነ ግን በቀጣዩ የሥራ ቀን በኩባንያው ዋና መ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ እና በኩባንያው ድህረ ገፅ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

## 10. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ስላለመሆኑ

10.1 ይህ መመሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

- ሥራ ላይ ካሉ የቦርድ አባት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአገልግሎት ዘመናቸው ከማብቃቱ በፊት በጠቅላላ ጉባኤ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሥራቸው እንዲነሱ ከተደረገ፣
- ሥራ ላይ ካሉ የቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በገዛ ፍቃዳቸው ከቦርድ አባልነት ከለቀቁ፣

- ሥራ ላይ ካሉ የቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በተለያዩ ምክንያቶች በቦርድ አባልነት መቀጠል ካልቻሉ ወይም፣
- በምልመላና አስመራጭ ኮሚቴው የቀረቡ እጩ ተጠቋሚዎች ከ50% በላይ በሆነ ድምፅ በጉባኤው ካልተደገፉ፣

10.2 በአንቀፅ 11.1 ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

10.3 በስራ ላይ ያሉት የቦርድ አባላት ከግማሽ በታች ከሆኑ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ በማድረግ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡

11. <u>ዝርዝር መመሪያ ስለመዘጋጀት</u>

የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ለዚሁ መመሪያ ተፈፃሚነት ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት ይችላል፡፡

12. <u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሀገሪቷ ህጎችና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

13. <u>ማሻሻያ</u>

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ሊሻሻል ይችላል፡፡ ሆኖም ማሻሻያው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካወጣቸው መመሪያዎች ጋር ተፃራሪ መሆን የለበትም፡፡

14. <u>የተሻሻለውን መመሪያ በጥብቅ ስለመፈጸም</u>

የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ የጸደቀውን የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ (ማሻሻያ 1) በጥብቅ እንዲፈጸም ያደርጋል፤ ራሱም በጥብቅ ይፈፅማል፡፡

15. <u>ተፈፃሚነት</u>

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ የአፈፃፀም መመሪያ በጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ ከፀደቀና በሚመለከተው መዝጋቢ አካል ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**